የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

# ኅብረቱና የጥምረት አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) ከተመሠረተ እነሆ ድፍን አምስት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ኅብረታችን ከምሥረታው ማግሥት ጀምሮ ሁለት አባል ድርጅቶች ኅብረቱ ሲቋቋም "አሳፋሪና ዘግናኝ" ብለን የፈረጅነውን የአገራችንና የሕዝባችን ሁኔታ ባላስተባቃና ባልተጠበቀ መልክ በመነጠላቸው፣ በአገራችን አዲስ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እውን እንዲሆን በአዲስ መንፈስ በተጀመረው ጠንካራና አንድ ወጥ የተቃዋሚው ጎራ ወሳኝ የጋራ ትግል ላይ አሉታዊ ጫና ማስከተሉ ይታወቃል፡፡ ሆኖም የቀሩት አባላት የኅብረቱን ትግል በቁርጠኝነት በመቀጠል የጠበቀውንና የተጠበቀውን ያኽልም ባይሆን ቢያንስ ለአንዲት አገርና ለሕዝቧ በመቻቻልና በመከባበር በልዩነት አብሮ መሥራት ብቻ ሳይሆን ውጤት ያለው ትግል ማድረግ እንደሚቻል አስመስክሯል፡፡

ዞሮ ዞሮ ኅብረታችን አንድ ወጥ ሳይሆን ልዩ ልዩ የፖለቲካ መርኃ-እቅዶች (ፕሮግራሞች) ያነገቡና የተለያየ ተመክሮ ያላቸው ድርጅቶችን ያቀፈና እነሱንም በመለስተኛ መርኃ-ግብር (ፕሮግራም) ያስተሳሰረ ስለሆነ ምርጫ ዘጠና-ሰባትን ተከትሎ በአገራችን የተከሰተው አጠቃላይ የሁኔታ ለውጥ የሚጠይቀውን ምላሽ በተመለከተ ኅብረታችን በውስጡ የአስተሳሰብና የአመለካከት ጤናማ ትግል ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ከሥራ-አስፈጻሚ አካል (ኮሚቴው) ሳምንታዊ መደበኛ ስብሰባዎች ውጭ የኅብረቱ ከፍተኛ አካል (ብሔራዊ ምክር ቤት-ሸንጎ) ሦስት አስቸኳይና ሁለት መደበኛ ጉባዔዎችን በማካሄድ በጉዳዩ ላይ በጥልቀትና በስፋት ተወያይቷል፡፡

ኅብረታችን ለተለወጠው የአገራችን ሁኔታ መጣኝ የሆነ የአስተሳሰብ ለውጥና በሱም ላይ የሚመሠረት የአሰላለፍና የአወቃቀር ሽግሽግ በማድረግ ሕዝብንና አገርን ያስቀደመ እርባና ያለው ትግል ማድረግ እንዲችል ብቁ ሆኖ እንዲገኝና አመራር እንዲሰጥ ከአባል ድርጅቶች ልዩ ልዩ አማራጭ አሳቦች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ ይኸን የኅብረታችንን ይዞታና የወደፊት የትግል አቅጣጫ የሚወስን ዓቢይ ጉዳይ በሰኔ ፳፩ እና ፳፪ ቀን ፪ ሺህ ዓ/ም የተካሄደው የኅብረቱ ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሦስተኛ መደበኛ ጉባዔ በዋና የመወያያ ነጥብነት (አጀንዳነት) አይቶና በጥልቀት መርምሮ ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ የኅብረቱ ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሦስተኛ መደበኛ ጉባዔ ኅብረቱ ለተለወጠው የአገራችን ሁኔታ መጣኝ ትግል ማድረግ እንዲችል በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 8 መሠረት ደንቡን አሻሽሎ አወቃቀሩ በጥምረት እንዲሆን በሙሉ ድምፅ ወስኗል፡፡ (ሥርዓቱን ተከትሎ የተሻሻለው መተዳደሪያ ደንብ የሚከተሉት አንቀጾች ላይ ለውጥና ማሻሻያ አድርጓል፤ 1.1፣ 3.2፣ 5.1.1፣ 5.2፣ 5.3.1፣ 5.4.1፣ 6.1.1፣ 6.1.9፣ 6.2፣ 6.3.2፣ 6.3.5፣ 6.9፣ 6.13.1.2፣ 6.13.1.4፣ 6.13.1.15፣ 6.13.2፣ 6.13.3.4፣ 6.13.4.11፣ 6.13.5.7፣ 6.14፣ 7.1.5 ).

ለመሆኑ ጥምረት ምንድን ነው? ለምንስ አስፈለገ? ኅብረቱ በቆየው አወቃቀሩ መሥራት ያልቻላቸውና አሁን በጥምረት አወቃቀር ማከናወን የሚችላቸው ምንድን ናቸው? ወዘተ.. ለሚሉ አግባብነት ያላቸው ጥያቄዎች ቀጥለን መልስ እንሰጣለን፡፡ <u>ከሁሉ በፊት ግን ግልጽ ማድረግ የምንፈልገው ነጥብ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) አሁን በውስጡ ያደረገው ለውጥ አወቃቀሩንና እሱን ተከትለው የሚስተካከሉ ተግባሮች ቅደም ተከተልን እንጂ ስሙንም ሆነ አርማውን እንዳልሆነ ነው፡፡</u>

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊቆጣጠራቸው ባልቻሉ ፀረ~ዴሞክራሲ ሥርዓቶች በተለይ በደርግና ከዚያም በኢሕአዴግ የግፍ አገዛዝ የተነሳ ዘግናኝና አሳፋሪ ሁኔታ ላይ እንዲወድቅ ተገደዋል፡፡ ይኸ ሁኔታ አገራችንን ዘርፈ-ብዙ ወደሆነ የችግር ማጥ ውስጥ ከቷት መቆጣጠር ወደማንችለው አደገኛ ሁኔታ እያመራች መሆኗ ለሁሉም ግልፅ ነው፡፡ ይኸን የስቃይና የውርደት ኑሮ ለመለወጥና በሕዝባችን ያልተገደበ ተሳትፎ የሚገነባ ፍትኀዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለማምጣት በነዚሁ የግፍና የአፈና ዓመታት ውስጥ በየአጣጫው ከባድ ትግል መካሄዱ በሁሉም ዘንድ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ትግሉ ሕዝባችን የተመኘውን ለውጥና እኛም ያቀድነውን ግብ ሊያስገኝልን አልቻለም፡፡

ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73796
Washington DC 20056-3796, U.S.A

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague, Netherlands
ስልክ Tel/Fax 31 70 394 6132

ለምን? ይኸን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ የሁላችን ኃላፊነት ነው። ግልፅና የማያሻማ ትክክለኛ መልስ ካልተሰጠበት ደግሞ ትግሉ ሌላ ረጅም ዓመታት ሊያስቆጥር ካልሆነ በስተቀር ወደፊት ፈቀቅ አይልም። ከምንገኝበት አዙሪትም መውጣት አንችልም። በቅድሚያ አገራችን አሁን በምትገኝበት ዘግናኝና አሳፋሪ ሁኔታ ላይ የወደቀችው ሕዝብ ያልመረጣቸውና የማይቆጣጠራቸው አንዴ በመለኮት፣ ሌላ ጊዜ በጉራዴ፣ አሁን ደግሞ በመከፋፈልና በአመፅ የሚያምኑ የሕዝብን ልዕልና የማይቀበሉ ስግብግብ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች እንደምንም ሥልጣን ይዘው ለግል ጥቅማቸውና ክብራቸው ሲሉ ከሕግ በላይ ቆመው እራሳቸውን ሕግ-በማድረግ ረግጠው በጥሬ ጉልበት ስለሚገዙን ነው። ይኸ ዓይነቱ ሥርዓት በምንም ተዓምር ሰላምና መረጋጋት፣ ፍትኅና የሕግ የበላይነት፣ እኩልነትና እድገት ሊያመጣ አይችልም። አገራችን እስካሁን ድረስ በሚያሳፍር መልኩ የለማኝ አገር የሆነችው ይኸ ዓይነቱ ሥርዓት እንደ መዥገር ስለተጣበቀባት ነው። የዚኸ ዓይነቱ ሥርዓት ካልተወገደና በምትኩ ሕዝብ በነፃ ምርጫውና ፍላጎቱ የሚቆጣጠረው በሕግ የሚገዛ ሥርዓትና አመራር እስካልተበጀ ድረስ ከጉስቁልናው አዙሪት መውጣት አይቻልም።

እንግዲህ ሥር ለሰደዱ ችግሮቻችንና ለነሱም ተጠያቂ የሆነውን የአምባ-ገነኖች የአገዛዝ ሥርዓት አዙሪት ለማስወገድና በምትኩ የጋራ ፍትኀዊ ሥርዓት ለመመሥረት ምን መልክ የያዘ ትግል ያስፈልጋል? ይኸንን ከባድ ጥያቄ ለመመለስ ሁለት ዓበይት ጉዳዮችን አያይዞ ማየት የግድ ይለናል።

1ኛ/ ዓላማችን 2ኛ/ አደረጃጀታችን

1ኛ/ ዓላማችን በኅብረቱ ዝርዝር የፖለቲካ መርኃ-እቅድ (ፕሮግራም) እንደተመለከተው ሁሉ ግልጽ ነው። ይኸውም ባጭሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዕድሉ ወሳኝ የሚሆንበት ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት መመሥረትና በሕግ የበላይነት መተዳደር ነው። በዚኸ ሥርዓት ሁሉም በእኩልነት ተጠቃሚ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አገራችን ዘለቄታ ያለው የሰላምና የዕድገት ጎዳና የምትይዝበት አማራጭ የሌለው መንገድ እንደሆነ እምነታችን ነው። ስለዚህ ይኸ የጋራ ዓላማ በጋራ አስተዋፅዖ የሚገነባ፣ ለኢትዮጵያችን መታደግና ለሕዝባችን ነፃነት መጎናፀፍ ቅድመ ሁኔታ ነው። ይኸ ምዕራፍ የፖለቲካ ድርጅት፣ የሲቪክ ማኅበርና ግለሰብ ሳይለይ ሁሉም እንደ አንድ አካል ሆኖ ታግሎ የሚያከናውነው የአገር ኅልውናና የፖለቲካ ሕይወትዋ ምሰሶ ነው። ይኸን ምሰሶ ሳያቆሙ ለፖለቲካ ሥልጣን መሽቀዳደም ወቅቱን ያልጠበቀና አቅጣጫ የሳተ አጉል አካሄድ በመሆኑ ውጤቱም ሕዝብን የመብቶቹ ባለቤት የማያደርግና የጉስቁልንናና የመከራ አዙሪቶች እንዲቀጥሉ የሚያደርግ እንደሆነ ካለንበት ሁኔታ መገንዘብ አያዳግትም። ከዚህ ግንዛቤ ስንነሳ የኅብረት ትግላችን በግልፅ ለተቀመጠው ዓለማ መሣካት የሚጠይቀውን ቅድሚያና ልዩ ትኩረት በመስጠት መረባረብ ያስፈልጋል። ቅድምያ ሰጥቶ መታገል ሲባል ሁሉም እንቅስቃሴዎች ለዚኸ የጋራ ትግል በሁሉም ረገድ ቅድሚያ መስጠት ብቻ ሳይሆን ለጋራ ዓላማው እውን መሆን የጥምረቱ አወቃቀር ለሚጠይቀው ሁሉ ተገዥ መሆን አለባቸው ማለት ነው። ለነፃነታችንና እድገታችን ቅድመ-ሁኔታ ነው ያልነውን የጋራ ዓላማ በዚህ መልክ ካላስተናገድነው እስካሁን የዘለቅንበትንና የተያያዝነውን ዓይነት አዙሪት ውስጥ ልንዘፈቅ ነው። አገራችን ማንም ቡድን እንደምንም ሥልጣን ላይ እየወጣ የሚጨፍርባት ሥርዓት-አልባ አገር ሆና ልትቆይ ነው። ይኸ ያለንበት አሳፋሪ የትርምስ ሁኔታ ላንዴና ለዘለቄታው እንዲያከትም ከተፈለገ የግለሰብ ሳይሆን የሕግ ልዕልና የነገሰበት ለሁሉም እኩል የሆነ ዴሞክራስያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት መኖር ይኖርበታል። ይኸ ዓይነቱ ሥርዓት በአንድ/ሁለት ፓርቲ በጎ ፈቃድ የሚመጣና የሚቸር ሳይሆን በጋራ ተሳትፎና ትግል የሚገነባ ከባድ ግን ደግሞ መተኪያ የሌለው ሥራ ነው። በኛ እምነት ሁሉም ዴሞክራሲና አንድነት ፈላጊ ኃይል ሁሉ (ፖለቲካ ድርጅት፣ ሲቪክ ማኅበር፣ ወዘተ... ባጠቃላይ ሰፊው ሕዝብ) የሚሳተፍበት፣ እንደየሁኔታው ማንኛውንም ሰላማዊና ሕዝባዊ የትግል ስልቶችና ትልሞች (ስትራቴጅዎች) ሊያጠቃልል ስለሚችል ትግሉን የሚያስተባብር ጠንካራ ማዕከል ያስፈልገዋል ማለት ነው። እንደዚህ ዓይነቱን ከባድ ኃላፊነት የሚጠይቅ ውስብስብ ሥራ ደግሞ በላላ አዘቦታዊ አደረጃጀትም ሆነ በተበታተነ መልክ ለአዎንታዊ ውጤት ማብቃት አይቻልም። ይኸን ስንል አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሁሉ አሁን ኅብረቱ በያዘውና በተከተለው የጥምረት አወቃቀር ካልተጠቃለሉ መታገል አይቻልም የሚል ግልብ አመለካከት የለንም። በአኳያው ኅብረቱ አወቃቀሩንና አደረጃጀቱን ወደ ጥምረት ከፍ ለማድረግ መወሰኑ ሌሎች ድርጅቶች እንዲከስሙ የሚያደርግና ድርጅታዊ ኅልውናቸውን እንደሚፈታተን አድርገው ማቅረብ የሚፈልጉ አይጠፉም። የዚኸ ዓይነት ግብዝ አመለካከት ግን ኅብረቱ የተከተለው የጥምረት አወቃቀር ለምንና

እንዴት እንደሆነ በውል ካለመረዳትና ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ የሚሰነዘር አመለካከት ከመሆን አያልፍም፡፡

ኅብረቱ የተቀበለው የጥምረት መዋቅር የሚሠራውና ገዥነት የሚኖረው አሁን የኅብረቱ አባል በሆኑትና ወደፊት የዚኽን ዓላማ ጠቃሚነት በሚቀበሉ ድርጅቶች ላይ ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪ ዝቅ ብለን እንደምንገልጸው ይኽ የጥምረት አወቃቀር ኅብረቱ ከሌሎች ድርጅቶች ጋር የአገርንና የሕዝብን ዓላማዎች እውን ለማድረግ የሚያደርገው ትብብር ላይ አበረታችና ገንቢ አስተዋጽዖ እንጂ አንዳችም አሉታዊ ገጽታ አይኖረውም፡፡

2ኛ/ እንደሚታወቀው ድርጅታችን የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ) የተቋቋመው የትግል ስልቱን ሕጋዊና ሰላማዊ እንደሆነ በመቀበልና ምርጫን እንደ መታገያ መሣሪያው ቆጥሮ ነው፡፡ የተደራጀውና የተዋቀረውም በዚሁ መንፈስና መሠረት ነው፡፡ ይሁንናም ድኅረ-ምርጫ ዘጠና-ሰባት የሰፈነው በከፋ መልኩ የተለወጠ ሁኔታ ኅብረቱ ሲመሠረት እታገልበታለሁ ያለው ሕጋዊ ሁኔታ በሕወሓት/ኢሕአዴግ አገዛዝ በአፍ-ጢሙ ተደፍቶ፣ እንኳን ተቃውሞን በሕጋዊ መልክ ማስተናገድ ቀርቶ እጅግ መሠረታዊ የሚባሉ ሰብዓዊ መብቶች እየተጣሱ ያሉበት ሁኔታ በመከሰቱ ኅብረታችን በጥር ፰ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ/ም ባካሄደው ሁለተኛ አስቸኳይ የብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ጉባዔ አገራችንና ሕዝባችን 'በአሸባሪ አምባ-ገነን' አገዛዝ ሥር መሆኗንና ኅብረቱም ለዚህ የተለወጠ ሁኔታ መጣኝ ትግል እንዲያደርግ፣ እራሱን ብቁ ማድረግ እንደሚጠበቅበትና እንደሚኖርበት ወስኗል፡፡ በዚሁ መንፈስ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ኅብረቱ እራሱ አሸባሪ አምባ-ገነን ብሎ የፈረጀውን አገዛዝ መታገል የሚችልበትን መንገድና ይኽንንም በተግባር መተርጎም የሚያስችለው አወቃቀርና አሰላለፍ እንዲይዝ ጥናቶችና ውይይቶች ሲደረጉ ቆይተዋል፡፡

የተሰበጣጠረውንና ውጥንቅጡ የወጣውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የዴሞክራሲና የመልካም አስተዳደር የመብት ትግል መልክ ለማስያዝ የተቋቋመው ኢዴኃኅ የአመለካከትና የራእይ፣ የፕሮግራም ጥራትና ደጋፊ ሳይገደው ቆራጥ አመራርና ግልጽ አሠራር አጥቶ ሕዝባችን የተያያዘው ሰላማዊ ትግል ድኅረ-ግንቦት ፈተና ውስጥ ሲገባና ለአረመኔዎች ጨካኝ ዱላ ተዳርጎ ተስፋው እንዲኮስስ ሲደረግ በሃዘኔታና በአቅመ-ቢስነት ተመልካች መሆን ሳይሆን እንደማንኛውም ኃላፊነት መውሰድ ያለበት የፖለቲካ ድርጅት ኃላፊነት ተቀብሎ አገሪቱንና ሕዝቧን ከአጣብቂኝ ለማውጣት አጥብቆ መሥራት እንደሚጠበቅበትና ግዴታም እንዳለበት፣ ከዚህ ታሪካዊ ኃላፊነት እራሱን ሊያገል ፈጽሞ እንደማይቻለው፣ ይኽንን አገራዊና ብሔራዊ ኃላፊነት መወጣት ካቃተው ግን አንገቱን አሸዋ ውስጥ ቀብሮ ቀን መቁጠር ወይም ሚሸሾ መጥፋትን ከመምረጡ በፊት አቅመ-ቢስና እርባና እንደሌለው ግልጽ መሆን እንደሚኖርበት ከአባል ድርጅቶች ውትወታ ሲደረግና ማሳሰቢያ ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

ይሁንናም ድኅረ-ምርጫ ዘጠና-ሰባት በተለይም የቅንጅት መሪዎች ወደ እስር ከተወረወሩ በኋላ በተቃዋሚው ጎራ በተከሰተው ችግርና ትግሉ በገጠመው የሁነኛ አመራር እጦት ኅብረቱ የሚጠበቅበትና የሚችለውን በማድረግ ትግሉን ማስተባበር አለመቻሉ ግልጽ ነበር፡፡ በመሆኑም ኅብረታችን ለተለወጠው የአገራችን ሁኔታ መጣኝ ትግል ማካሄድ እንዲችል ልዩ ልዩ የአደረጃጀትና የአወቃቀር አሳቦች በውስጡ ተንሸራሽረዋል፡፡ በዚህም አሁን ኅብረቱ ባለው ይዞታ ይቀጥል ከሚለው እስከ ውኅደት ድረስ በአማራጭነት ቀርበዋል፡፡ አሁን ባለበት ማለት ለሕጋዊ ትግልና ለምርጫ ፖለቲካ በተዋቀረበት ይቀጥል የሚለው እሳብ አባላት ከየድርጅቶቹ ተውጣጥተው የሚሠሩበት በመሆኑና የተለወጠው ሁኔታ ከፍተኛ ምስጢራዊነትን፣ ሥነ-ሥርዓትንና መተማመንን የሚጠይቅ ትግልና ያንንም ለማድረግ የሚያስፈልገውን ጠበቅና ጠበብ ያለ አወቃቀር የግድ እንደሚል ያላገናዘበ በመሆኑ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በአኳያው ውኅደት የሚለውም ምንም እንኳ አገራችን እንደ አገር ሕዝባችንም እንደ ሕዝብ የኅልውና ፈተና ላይ መሆናቸውን ሁሉም የተቀበለውና በዚህ ሁኔታ ደግሞ የግል ድርጅት ኅልውና ከአገርና ከሕዝብ በላይ ሆኖ መታየት እንደማይችል ግልጽ ቢሆንም፣ ተናጠል አባል ድርጅቶች በዚኽ የውኅደት ጎዳና ቢያመሩ ኅብረቱ እንደሚደግፍና እንደሚያበረታታ በመግለጽ ሆኖም በአሁኑ ጊዜ የአባል ድርጅቶችን ታሪክና ሁኔታ በማጤን ሁሉም የየግል ድርጅታዊ ኅልውናችሁን አጥታችሁ ተዋኃዱ ብሎ ማስገደዱ ተግባራዊ የሚሆንም ሆነ የግድ አስፈላጊ ሆኖ ስላልተገኘ አሳቡ ውድቅ ሆኗል፡፡ ሆኖም ከውኅደት መለስ ኅብረቱ ከምሥረታው ጀምሮ እስካሁን ከተከተለው ለሕጋዊ ትግል ታስቦ ተግባር ላይ ከዋለ የላላ አደረጃጀትና አወቃቀር ጠበቅና ጠበብ ያለ አወቃቀር የመከተሉ አስፈላጊነት ታምኖበታል፡፡
ይኽንን ለተለወጠው የአገራችን ሁኔታ መጣኝ ትግል ለማድረግ የተሻለ መሆኑ የታመነበት አደረጃጀት ጠበቅና ጠበብ ያለ አወቃቀር ጥምረት ብለን ሰይመነዋል፡፡ በዚህ የጥምረት አወቃቀር የኅብረቱ ሥራዎች የሚሠሩት እስካሁን በኅብረቱ ውስጥ በቆየው አሠራር ዘይቤ ከየድርጅቶቹ ተውጣጥተው በሚቋቋሙ አካሎች (ኮሚቴዎች) አማካይነት ሳይሆን አመኔታን፣ ፈቃደኝነትን፣ ብቃትንና ችሎታን ብቻ በጠየቀ ሁኔታ ይሆናል፡፡ ይኽም ማለት ማንኛውም የኅብረቱ ሥራ ለሥራው ብቃት ባለው(ባላት) ማንኛውም የኅብረቱ አባል ድርጅት አባል (አባላት) ወይም አባል ድርጅቶች አባላት አማካይነት ይከናወናል ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ኅብረቱ በየትኛውም አካባቢ ለየትኛውም የሥራ መስክም ሆነ ግዳጅ ማንኛውም ድርጅት ወይም ድርጅቶች እንደ ተናጠል ድርጅት ወይም ድርጅቶች ሆኖ/ሆነው ሳይሆን እንደ ኅብረት ሆኖ/ሆነው የኅብረቱን ተልእኮ መወጣት ይችላል/ይችላሉ፡፡ ይኽ አወቃቀር መተማመንን በከፍተኛ ደረጃ

የሚጠይቅና ተጠሪነትና ተጠያቂነት ከተናጠል ድርጅቱ ወደ አጠቃላይ ኅብረቱ የሚሰጥ አሰላለፍ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ይኸም ስለሆነ ነው የኅብረቱ አባል ድርጅቶች የጥምረትን አወቃቀር በመቀበል ኅብረቱን ወደላቀ ድርጅታዊ ትስስር አሳድገውታል የምንለው፡፡ ስለሆነም ጥምረት የኅብረቱ የአደረጃጀት ባህሪ እንጅ አዲስ የኅብረቱ ስም አይደለም፡፡

ይኸ የመዋቅር መስተካከል ጥያቄ በኅብረቱ ውስጥ የኅብረቱን ዴሞክራሲያዊ የጋራ አሠራር ዘይቤዎችን በመከተል ረዘም ላለ ጊዜ ያወያየ ጉዳይ ነው፡፡ በአገር ደርጃ የጋራ ሥርዓት በጋራ ታግለንና ተስማምተን መፍጠር ስላልተቻለ መከራችን እንደበዛ ግልጽ ነው፡፡ በእርግጥ ኅብረቱ ሲመሠረት ይዞት የተነሳው እምነት (የምርጫ ፖለቲካን ዋና ማጠንጠኛው ያደረገ ሕጋዊ ትግል)፣ አወቃቀርና አሠራር (ይኸንኑ ይዞት የተነሳውን እምነትና እምነቱን አስፈጽምበታለሁ ብሎ የያዘውን ተቀዳሚና ብቸኛ የትግል ስልት የተከተለ) ይዞታ ላይ ሆኖ በዓይነትም ሆነ በይዘት ለተለወጠው የአገሪቱ ሁኔታ አመርቂ ምላሽ እሰጣለሁ ብሎ ማሰብ የማይሆን ብዥታ እንደሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ድሎች መቀልበስ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ የኅብረቱ አባላት ሲያስገነዝቡ ቆይተዋል፡፡

ለጋራ ዓላማ በጋራ መሰለፍና መሠማራት አስፈላጊ ሆኖ እያለ የኅብረቱ ኃይል አንዴ ለኅብረቱ ሌላ ጊዜ ለየድርጅቱ 'የመንታ እናት...' እንዲሉ በሁለት አቅጣጫ (አንዴም ተፎካካሪ ሌላ ጊዜም ተጠላላፊ) ሆኖ ሲንገዋለል ቆይቷል፡፡ ኅብረቱ ለነደፈው የጋራ ዓላማ ቅድሚያ ሰጥቶ ትግሉን መግፋት ሲገባው፣ የኅብረቱ አንቀሳቃሽ ኃይል የሆኑት አባል ድርጅቶች በአንድ አገራዊ ዓላማ ተጣምሮ እንደ አንድ ድርጅት ሆኖ መታገል ሲኖርባቸው፣ በተናጠል ለየግል ድርጅቶቻቸው ሥራ እኩል ወይም የበለጠ ትኩረት በመስጠታቸው የኅብረቱን ትግል በተለይም የድኅረ-ግንቦት ሁኔታ የጠየቀውን የጋራና አንድ-ወጥ እርብርብ አለማድረጋቸው ትግሉን በማዳከሙ ረገድ አስተዋጽዖ አድርገዋል ማለት ይቻላል፡፡ ለግል ድርጅት ዝና ወይም ልዕልና ሊጠቀሙበት የሞከሩም አይጠፉም፡፡ በዚህና በመሳሰሉ ምክንያቶች ኅብረቱ ወደ አቀደው የጋራ ሕዝባዊ ግብ ለመጓዝ ጉልበት አጣ፣ እንቅፋትም በዛበትና ባለበት ሄደ፣ እንዲያውም እርባናው ቀነሰ፣ ኮሰመነ፡፡ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የቆየው የኅብረታችን አወቃቀርና አደረጃጀት የየድርጅቱን መዋቅር እንዳለ ስላቀፈና ለጋራው ዓላማና ሥራ ከየድርጅቱ ትንሽ ትንሽ ተቀንሶ በሚደረግ ልገሳ ስለሆነ የሚከናወነው በሁለቱ መዋቅሮች መካከል ለሚኖረው ልዩነትና አንዳንዴም ለሚከሰተው መጠላለፍ ቀጥተኛ አስተዋጽዖ ነበረው፡፡ ለምሳሌ በአንድ የጋራ አገራዊ ጉዳይ ላይ በኅብረቱ አንድ መግለጫ ይወጣና እሱን ተከትሎ ደግሞ አንድ አባል ድርጅት በዚያው ጉዳይ ላይ ሌላ መግለጫ፣ አንዳንዴም ተፃራሪ አመለካከቶችና አስተሳሰቦችን በያዘ መልኩ ይወጣል፡፡ በዚኸም ኅብረቱና አባላቱ አንድ ዓላማና ተመሳሳይ አመለካከት የላቸውም እንዴ? ይባላል፡፡ ወይም ለአንድ የኅብረቱ ሥራ (ከባድ መስዋዕትነትን የሚጠይቅም ሊሆን ይችላል) ሰው ይመደብ ሲባል "የኔ ድርጅት አላመነበትም" ብሎ የጋራ ሥራው አጉል እንዲቀርም ይደረጋል፡፡ ይኸ አካሄድ የአስተሳሰብና የትስስር ዝንፈት እንደፈጠረ ግልጽ ነው፡፡ የሕዝብ ድምፅ ባልተከበረበትና በተሰረቀበት ሁኔታ ከሌሎች ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋራ በጋራ ሳንወስን "ፓርላማ" ውስጥ አንገባም ብሎ ኅብረቱ ሲወስን "የኔ ድርጅት ይካፈላል" ብለው ያፈነገጡ አባል ድርጅቶች እንደነበሩም ይታወቃል፡፡ ይኸ ሁሉ ሲሆን ግን ሁሉም "ለኅብረቱ ዓላማ ቅድሚያ እሰጣለሁ" እያለ ነው፡፡ በዚህ የጥምረት አደረጃጀት ግን ሁሉም አባል ድርጅቶች ለጋራው ውሳኔ ተገዥ ሆነው ለኅብረቱ ሥራ እንደ አንድ ድርጅት በአንድ ማዕከል (እዝ) ሥር ስለሚሠሩ የተጠቀሱትና ሌሎች ተመሳሳይ አጉል ምክንያቶችና መሰናክሎች ይወገዳሉ፡፡

በኅብረቱ ውስጥ የጥምረት አደረጃጀትና የሕዝባዊ ትግል ስልት አስፈላጊነት ለሦስት ዓመታት ያኸል ውይይት ሲደርግባቸው ቆይቷል፡፡ በመጋቢት ወር ፳፱ ዓ/ም (Apri 2007) በተሠየመው የኢዴኃኅ ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ጉባዔ ልዩ ኮሚሽን ተቋቁሞ ብዙ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ የደቡብ አፍሪቃው (ANC) ፀረ-አፓርታይድ ትግል እንደ አዎንታዊ ተመኵሮ፣ እስካሁን ያልተሳካው የፍልስጥኤም (PLO) አሉታዊ ተመኩሮ፣ ወዘተ... በስፋት ተጠንተው ቀርበው ብዙ ካወያዩና በቂ ግንዛቤ ከተገኘ በኋላ የአገራችን አሳሳቢ ሁኔታ እንዳይባባስ የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ እንዲቻልና ኅብረቱ የቆመላቸው ሕዝባዊና አገራዊ ዓላማዎች ፍሬ እንዲሰጡ ከተፈለገ ለኅብረቱ እንቅስቃሴ ቅድሚያ መሰጠት አለበት የሚል አጠቃላይ እምነት በሁሉም አባል ደርጅቶች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ ቢመስልም በተግባር አዋዋሉ ላይ ሠፊ ልዩነት ነበር፡፡ ሁለት አባል ድርጅቶች የጥምረት አደረጃጀት የግል ድርጅትን መብት ይጋፋል፣ የግል ድርጅትን እንቅስቃሴ ይገታል፣ ድርጅትን ያጫጫል፣ ወዘተ... የሚሉ ምክንያቶች በማቅረብ የቀረበውን አማራጭ አወቃቀር ሲቃወሙ ሌሎች አባል ድርጅቶች ደግሞ በአንፃሩ ይፋዊ እንቅስቃሴ ካልሆነ በስተቀር የውስጥ ድርጅታዊ ሥራ (ምልመላ፣ የአባላት ስብሰባ፣ ወዘተ...) አይታገድም፣ ለአገር-አድን ሥርዓት ሲባል የተወሰነ ድርጅታዊ መብትን ፈቅዶ ቆርሶ ለኅብረቱ መስጠት ደግሞ መብት መጋፋት ሳይሆን

*የሁሉንም መብት የሚያስከብር ሥርዓት ለማምጣት ለሚደረግ ትግል የሚከፈል መጠነኛ ድርጅታዊ መስዋዕትነት እና አስፈላጊ አስተዋፅዖ ሆኖ ሊቆጠር ይገባል፣ ሁሉም ድርጅቶች በሕዝባቸው መኻል በነፃነት መንቀሳቀስ የሚችሉበት ሁኔታ ሲፈጠር የየግል ድርጅት ሥራ ላይ መጠመድ ይቻላል፣ አሁን የሚደረገው ትግል ሕዝብንና አገርን ከትርምስ ለማዳንና ብሎም ለድርጅቶች አመች ሁኔታን ለማስገኘት ነው፣ ወዘተ... በሚል ለጋራው ትግል ቅድሚያ እንዲሰጥ አበክረው አሳሰቡ፡፡ ኅብረቱ ለተለወጠው የአገራችን ሁኔታ መጣኝ አወቃቀር ይዞ እንዲታገል በአራተኛው አስቸኳይ የብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ጉባዔ ላይ በአባል ድርጅቶች መኻል የነበረው ክርክር እልባት ሳያገኝ በአንድ አባል ድርጅት (በኢሕአፓ) የሁለት ወር ጊዜ እንዲሰጠው የቀረበ ጥያቄ ምክንያት ጉባዔው በይደር ቢተላለፍም፣ ጉዳዩ ለስምንት ወራት እንደተንጠለጠለ ቆይቷል፡፡*

*በመጨረሻም በሥራ-አስፈጻሚ ኮሚቴው ሙሉ ስምምነትና ውሳኔ በኅብረቱ የወቅቱ ሊቀ-መንበር በአቶ ፋሲካ በለጠ የተጠራው የኅብረቱ ብሔራዊ ምክር ቤት (ሸንጎ) ሦስተኛ መደበኛ ጉባዔ ሰኔ ሃያ-አንድና ሰኔ ሃያ-ሁለት ቀን ፪ሺህ ዓ/ም ስድስት አባል ድርጅቶች በተገኙበት ተካሂዶ ኅብረቱ የጥምረት አወቃቀርን ተቀብሎና አፅድቆ "ዛሬ ትብብር ነገ ውድድር" የሚለውን የወቅቱን የትግል አቅጣጫና የመጪውን የጋራ ሥርዓት ገፅታ የሚጠቁም መፈክር አንግበው ለሥልጣን ሳይሆን ለሥርዓት ለውጥ ትግል ተሰልፏል፡፡ ይኸ የጥምረት አወቃቀር ያለውን ውስብስብና ዘርፈ-ብዙ የትግል አካሄድ ባልተዝረከረከና አመራሩም ጠበቅ ባለ ማዕከልነት ኃላፊነቱን እንዲወጣና ኅብረቱም የታቀደለትን ዓላማ ባጭር ጊዜ ውስጥ እግቡ የሚያደርስ አደረጃጀት ነው፡፡*

*ይኸ የአመራሩን ጠበቅ ያለ ማዕከልነት የሚጠይቅ አሰላለፍና አደረጃጀት አስፈላጊነቱ በብዙ አቅጣጫ ሊታይ ይችላል፡፡*

*ሀ/ የምንታገለው ክፍል ማዕከልነቱ የጠበቀ (ያውም እስታሊናዊ)፣ አደረጃጀቱም ከቀበሌ ወርዶ ንዑስ ቀበሌና መንግሥታዊ ቡድን በማለት እያንዳንዱን ቤተ-ሰብ (ቤት) የሚቆጣጠርበት መዋቅር የዘረጋ በመሆኑ በአንፃሩ ቢያንስ ያንኑ ያኽል ለትግሉ የጀርባ አጥንት የሆነ ሕዝባዊ አደረጃጀት እንደሚያስፈልግ አያጠያይቅም፡፡*

*ለ/ እስካሁን በቆየው የኅብረቱ አወቃቀር፣ ምንም እንኳ ፈቃደኛ የሆኑ ድርጅቶች አልነበሩም ባይባልም፣ እንደየግል ድርጅቶች ጠበቅ ያለ ማዕከልነት ባለመኖሩ በተለይ ድኅረ-ግንቦት ዘጠና-ሰባት የተለወጠው ሁኔታ የግድ የሚጠይቀውን አወቃቀር መከተል ባለመቻላችን ወሳኝ የሆነውን የጋራ ሥራ ቀን ተቀን በመከታተል፣ በመፈጸምና በማስፈጸም ማከናወን እንዳልተቻለ ይታወቃል፡፡ ይኸንን ስንል በአንደምታ፣ በይሆናል ወይም በምናልባታዊነት ሳይሆን በተግባር ሞክረን ስላየነው ነው፡፡ ኅብረቱ በተለይ የትግሉ ማዕከል በሆነው በአገር ውስጥ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ ሁኔታው የግድ በሚጠይቀው አሠራር እቅዶች አውጥቶ በተግባር ለመተርጎም አልቻለም፡፡ ይኸ የሆነው ደግሞ የአባል ድርጅቶች ፍላጎት ማነስ ስላለ ሳይሆን ሥራው ምን እንደሚጠይቅና በምን መልክ መደራጀት እንደሚያስፈልግ ተመሳሳይ ግንዛቤ ላይ መድረስ ባለመቻሉ ነው፡፡ በአንድ ድርጅት ውስጥ ባሉ አባላት መኻል እንኳ መተማመን በገደደበት የድኅረ-ግንቦት የቀውጢ ሁኔታ መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥና በጋራው ሥራ ላይ ለመረባረብ ተመጣጣኝ ቁርጠኝነትና ውሳኔ ሳይኖርና አስፈላጊው የመዋቅር ሽግሽግ ሳይኖር ሽብርተኛ አምባ-ገነን መንግሥትን ለመቋቋም ቢያንስ አስቸጋሪ እንደሆነ የአብዛኛው የኅብረቱ አባላት ግንዛቤ ነበር፡፡ በዚያን ወቅት ደግሞ የሕዝባችንን የግንቦት ድሎች ከቅልበሳ ለማዳን ከኅብረቱ ውጭ ያሉ አገር-ወዳዶችና ዴሞክራት ኃይሎች ሁሉ እንደገና በአዲስ መልክ በአስቸኳይ መሸጋሸግና መሰባሰብ እንደሚኖርባቸው ኢዴኃኅ ጥሪውን በይፋና በተደጋጋሚ ሲያስተጋባ የነበረበት ሁኔታ ነው፡፡ በኛ በኩል እንኳን ለሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት የመጣል ያኽልን ከባድ ሥራ ቀርቶ አሸባሪ አምባ-ገነን ብለን የፈረጅነው አገዛዝ በሕዝባችን ላይ የሚያወደውን ግፍ ለመቋቋም በቆየው አወቃቀር፣ መልክና አካሄድ አከናውናለሁ ብሎ ማሰቡ ራሱ የዋህነት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡*

*ኅብረቱ ይዞት በቆየው አወቃቀር ይቀጥል ማለት አንድም በኢትዮጵያ ውስጥ ኅብረቱ ሲመሠረት የነበረው ሁኔታ አሁንም እንዳለ መቁጠር፣ አለበለዚያም እንዲሁ ኅብረት አለ እየተባለ አንድም እርባና ያለው ትግል ሳያደርግ በሂደት እንዲከስም እጅን አጣጥፎ መጠበቅ ይሆናል፡፡ ኅብረታችን የጥምረትን አወቃቀር ተቀብሎ ፈርጀ-ብዙ የሆነውን ሕዝባዊ ሰላማዊ ትግል ለመታገል ቆርጠን በተነሳነው የኅብረቱ አባል ድርጅቶች ዘንድ ግን እጅ አጣጥፎ የኅብረቱን መክሰም መጠበቅም ሆነ የአገራችን ሁኔታ መቀየሩንና ለተቀየረው ሁኔታ መጣኝ አወቃቀርን ባለመቀበል ከአገርና ከሕዝብ ይልቅ ድርጅት ይቅደም የሚያሰኝ ኃላፊነትን ያለመወጣት አቋም ለመያዝ አልከጀልንም፡፡ በኅብረቱ ውስጥ የተካተትን ድርጅቶች ቢያንስ ላለፉት አምስት ዓመታት (አብዛኞቹ ከዚያም ረዘም ላለ ጊዜ) በአገራችን አምባ-ገነን አገዛዝ ተወግዶ ሕገ-መንግሥታዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን እንዲሆን በጋራ በመታገል የበለጠ*

መቀራረብንና መተማመንን ለማዳበር የተሻለ ዕድልና ልምድ ያገኘን በመሆኑ የተለወጠው የአገራችን ሁኔታ የግድ የሚጠይቀውን ከየድርጅቶቻችን በላይ የጋራችን ለሆኑ የአገርና የሕዝብ ዓላማዎች እራሳችንን የበለጠ በማስገዛት የጋራ ትግሉ ላይ እርብርብ በማድረግ ቅጥ ያጣ መሰነጣጠቅ የተጠናወተው ተቃዋሚ ክፍል በመሰባሰብ ሰፊ መሠረት ያለው የተቃዋሚው ጎራ እንዲፈጠር ግንባር ቀደምና ምሳሌአዊና እርባና ያለው ሚና መጫዎት እንዲችል ሕጋዊ ትግልና የምርጫ ፖለቲካን የመታገያ መርኁ አድርጎ የተዋቀረውን ኅብረታችንን በምእኩል አደረጃጀት ማዋቀሩ አስፈላጊ መሆኑን አምነን ነው በጥምረት እንዲዋቀር ያደረግነው።

ለመሆኑ ይኽ የጥምረት አወቃቀር ከአባል ድርጅቶቹ ከአሁን በፊት ከሚያደርጉት የተለየ የሚጠይቅባቸው ምንድነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። አዎን ይኽ የጥምረት አወቃቀር ከአባል ድርጅቶች የሚጠይቀው ኅብረታችን አሁንም እንቅስቃሴዎቹን በኅብረት ደረጃ ብቻ ማድረግ ስለሚጠበቅበት ቀደም ሲል እንደተገለፀው እንደ ሁኔታው በተናጠል ድርጅት ላይ የተሰነዘሩ ጉዳዮችን ለማብራራት ከሚሰጥ መግለጫና የአባላት ስብሰባ ከማድረግ ውጭ በአገራዊና አጠቃላይ ሕዝባዊ ጉዳዮች ላይ የተናጠል መግለጫ ከመስጠትም ሆነ ሕዝባዊ ስብሰባዎችና ሌሎች አገር-አቀፍ ይዘት ያላቸው ተግባራትን በጋራና በኅብረት ስም ብቻ እንጂ በተናጠል ድርጅት ማድረግ አይቻልም። በተቻለ መጠን በማንኛውም አባል ድርጅት ላይ የሚሰነዘር ዘመቻ ወይም ጥቃት በአጠቃላይ በኅብረቱ ላይ እንደተደረገ ስለሚቆጠር በሁሉም ረገድ ኅብረቱ አብሮ ይቆማል።

የኅብረቱ የጥምረት አወቃቀር እስከመቼ ድረስ የሚዘልቅ ነው? የሚል ጥያቄ እንደሚነሳ ግልጽ ነው። ከፍ ሲል እንደጠቀስነው ይኽ የኅብረታችን አዲስ አወቃቀር በአባል ድርጅቶች ዘንድ የተፈጸመ ውኅደት ሳይሆን ኅብረቱ የተጠናከረ ማእከላዊነት ባለው አሠራር የተለማቸውን ዓላማዎች ደረጃ በደረጃ እግብ ለማድረስ እንደ አንድ ድርጅት ሆኖ ለመንቀሳቀስ የሚጠቀምበት የትግል ጊዜ አደረጃጀት ነው። ይኽ አደረጃጀትም በየደረጃውና በየጊዜው በሚያስገኘው ውጤት እየተመረመረና እየተገመገመ አስፈላጊው ለውጥ የሚደረግበት የትግል መገልገያና መሣሪያ ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ በአገራችን መሠረታዊ የሥርዓት ለውጥ እንዳይመጣ በአሁኑ ጊዜ እንቅፋት የሆነው በአቶ መለስ ዜናዊ የሚመራው የሕወሓት/ኢሕአዴግ አሸባሪ አምባ-ገነን የነጋዴ ቡድን ብቻ ነው ማለት አንችልም። እሱማ የቆመለትን አፍራሽ ተልዕኮ እቅዱንና ትልሙን ቀጥ ብሎ እየሠራ ነው። እሱን በጭፍን የሚደግፉት የውጭ ኃይሎችም አይደሉም፤ እነሱም ከምንምና ከማንም በላይ ቅድሚያ የሚሰጡትን፣ እኛ በምንም መልክ እንፈርጀው በምን ዞሮ ዞሮ ብሔራዊ ጥቅማቸውን የማስጠበቅ ተግባራቸውን ነው እየሠሩ ያሉት። በእኛ እምነት የመጀመሪያውና ዋናው ተጠያቂ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፍነው በተለይም አገር-አቀፍ ራእይ አለን የምንለው ወገኖች ነን። ሕዝባችን በክቡር መስዋዕትነቱ በግንቦት ሰባት ቀን ዘጠና-ሰባት ዓ/ም ፍላጎቱን፣ አቋሙንና ውሳኔውን በይፋ አሳወቀን፣ የሥርዓት ለውጥ እንቅፋት ለሆነው አገዛዝ ጀርባውን ሰጠ፣ ድምፄን አታስሰርቁብኝ፣ ድሌን አስከብሩልኝ፣ መስዋዕትነቱን እከፍላለሁ፣ ታግላችሁ አታግሉኝ፣ ምሩኝ አለ። ታዲያ የድርጅቶች ምላሽ ምን ነበር? በቅድመ-ምርጫ ካሳየነው ውልክልክ ያለ አቋም በባሰ ዝርክርክ አልን፣ ብዙዎች ለአገዛዙ ጭዳ ሆኑ፣ የቀረነው እንኳን ትግሉን አስተባብረን ልንመራ ሕዝቡን በአግባቡ መከተል አልቻልንም። ይባስ ብሎ አገዛዙ የኢትዮጵያን መሬት ለባዕዳን አሳልፎ በመስጠት በልጆቿ ክቡር መስዋዕትነት ተከብሮ የኖረውን ድንበር እያስደፈረ ዜጎች ታፍነው ወደ ባዕድ ታግተው በመወሰድ እንዲሰቃዩ እየተደረገ ነው። ታዲያ በሕዝባችንና በአገራችን ላይ ይኽ ሁሉ እየሆነ በሌለ ሥልጣን መራኮትም ይሁን እንደ ጧት ጤዛ ለሚረግፍ ከንቱ ዝና ወይም ለድርጅት የበላይነት መሯሯጥ ተጠያቂ፤ ከተጠያቂም ዋና ተጠያቂ አያደርገንም? ይኽ እውነታ ነው የኅብረቱ አባላት ከድርጅት በፊት አገርና ሕዝብ መቅደም አለባቸው በማለት በጥምረት እንዲሰለፉ ያስገደዳቸው። ኢዴኃኅ የጥምረት አወቃቀርን አምኖ ሲቀበል እጅግ ለተወሳሰበውና ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ አስጊ እየሆነ ለመጣው የአገራችን ሁኔታ ብቻውን መልስ ሊሰጥ ይችላል የሚል ቀቢፀ-ተስፋ ኖሮት አይደለም።

ኅብረታችን አሁን በያዘውና በሚሠራበት የጥምረት አወቃቀር ሁለት ደረጃዎች ያለው እንቅስቃሴ ያደርጋል።

የመጀመሪያው በኅብረት ደረጃ የተለማቸውን እቅዶች እውን ለማድረግ እንደ አንድ ድርጅት ሙሉ ትኩረቱን ሰጥቶ በመንቀሳቀስና አመርቂ ውጤት ያለው ትግል በማድረግ አቅጣጫ የሳተው ትግል ፈር እንዲይዝና ሕዝባችን ቅድመ-ግንቦት የነበረውን የትግል ማዕከልነትና ባለቤትነት መልሶ በእጁ እንዲያስገባ ለማስቻል የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማበርከት፣

እና በሁለተኛ እረድፍ ከምሥረታው ጊዜ ጀምሮ ባለው እምነት መጠነ-ሰፊና ፈርጀ-ብዙ ለሆኑት የአገራችን ውስብስብ ችግሮች ዘለቄታዊነት ያለው መፍትኄ ማስገኛ መንገዱ ዓላማውና ግቡ ግልጽ በሆነና በመከባበርና በመርኅ ላይ በተመሠረተ ሁል-አቀፍና ሠረተ-ሰፊ የአገር-ወዳዶችና የዴሞክራት ኃይሎች መሰባሰብ አማካይነት በሚደረግ ሕዝብን ማዕከል ያደረገ ትግል የማካሄድ እምነቱ መሠረት

ይኸንን የኃይሎች መሰባሰብ ለማስገኘት የሚደረገውን ጥረት የተሻለ ትኩረት ሰጥቶ የበኩሉን ግንባር-ቀደም አስተዋጽዖ ለማድረግ ነው።

በዚህ ረገድ አንደኛ ከተናጠል ድርጅት ይልቅ የአገርና የሕዝብን ጥቅም በማስቀደም የኅብረቱን የጥምረት አወቃቀር የሚቀበሉ ድርጅቶች ኅብረቱን ተቀላቅለው የጋራውን ትግል እንዲያጠናክሩ ኢዴኃኅ የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል፣ ያበረታታል፣ ሁኔታውንም ያመቻቻል።
በልዩ ልዩ ምክንያቶች የጥምረቱን አወቃቀር መቀበል ከማይችሉም ሆነ ከማይፈልጉ ድርጅቶች ጋር በየደረጃውና እንደ ሁኔታው የጎን ግንኙነቶችን በማድረግ የአገር-ወዳዶችና የዴሞክራት ኃይሎች መሰባሰብ በአስቸኳይ እውን መሆን እንዲችል ያላሰለሰ ጥርት ያደርጋል፣ ግንባር ቀደም ሚና ለመጫዎት ተዘጋጅቷል።

ይኸን በተመለከተ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ካላቸው ወገኖች ጋር የጋራ እንቅስቃሴ ለማድረግ ኅብረቱ ዝግጁነቱን ሲገልጽ፣ መሠረተ-ሰፊ የሆነና ሁሉም አገር-ወዳድና ዴሞክራት ኃይል የሚካተትበት የአንድነትና የፍትኅ እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ሁኔታን የሚያመቻች አንድ አገር-አቀፍ የቀውጢ ጊዜ ግብረ-ኃይል (መብትና ኅልውና አስጠባቂ ግብረ-ኃይል) በአስቸኳይ ስለሚቋቋምበት ምክክር የሚያደርግና የሚያዘጋጅ አካል *(Steering Committee)* እንዲቋቋም በዚህ አጋጣሚ ጥሪውን ለሚመለከተው ሁሉ በማስተላለፍ ጭምር ነው።

ዛሬ ትብብር ነገ ውድድር!
ሁሉም ለአገር-አድን ትግሉ በጋራ ይቁም!!
የኢትዮጵያ ትንሳዔ በጋራው ትግል እውን ይሆናል!!!

**የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)**

**ሰኔ ፲ ቀን ፪ሺህ ዓ/ም**